# March 4 Freedom

Activism, Transparency, Accountability
www.march4freedom.org

## በአስቸኳይ የሚወጣ የድጋፍ መግለጫ

**መስከረም 13 ቀን, 2005 ዓ.ም**

ማርች ፎር ፍሪደም በሀገራችን የተንሰራፋውን አምባ ገነናዊ ስርዓት ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ መንግሎ በመጣል በምትኩ ዲሞክራሲያዊ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ሲባል በተለይም በሀገር ውስጥ ለነፃነትና ለፍትሕ የሚደረገው ህዝባዊ ትግልና መነሳሳት መደገፍ አማራጭ የለውም ብሎ በማመን በዲያስፓራው ሲንቀሳቀሱ ከቆዩት ነፃና አንጋፋ ሲቢክ ማሕበራት አንዱ መሆኑን ይታወቃል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከህዝቡ ጎን ተሰልፈው የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ሰላማዊና ሕጋዊ የትግል ስልት ተከትለው አምባ ገነኑን ስርዓት በመታገል ላይ ካሉት ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች አንዱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በህዝቡ ዘንድ ሰፊ ድጋፍና ተቀባይነት ያለው፣ በአደረጃጀቱ ለ20 ዓመታት ያህል በስልጣን ላይ የተፈናጠጠው አፋኝ አገዛዝን መተካት የሚችል ትልቅ አማራጭ ፓርቲ መሆኑን ከሚያደርጋቸው ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችና ከሚያራምዳቸው ዓላማዎቹ ለመገንዘብ ችለናል። መድረክ በቅርቡ በሰሜን አሜሪክ ከኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በዋና ዋና ከተሞች ሰፊ ህዝባዊ ስብሰባዎች ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩንም ይታወቃል።

ማርች ፎር ፍሪደም ከማንም ጋር ያልወገነና የማንም ሀይል ተቀጥላ ያልሆነ ለዲሞክራሲ፣ ለሰው ልጅ ሰብኣዊ መብትና ክብር የሚታገል ሲቪክ ድርጅት ቢሆንም በሀገር ውስጥ በተለይም በውጭ ሀገር በዲያስፓራው ያለው ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚመዝነው በሀገር ውስጥ ህዝቡ ራሱ የትግሉን ባለቤት ለማድረግ ለሚደረገው ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ካለው ፋይዳና አስተዋፀዖ አኳያ ነው። በዚሁ መሰረት ማርች ፎር ፊሪዶም የመድረክ የአመራር ልዑካን በሰሜን አሜሪካ የጀመሩትን የህዝብ ስብሰባዎች አባራታች፣ ተስፋ ሰጪና ለአጠቃላይ የህዝቡ ትግል ገንቢ አስተዋፀዖ ይኖሯል ብሎ ስለሚያምን የተጀመሩትን ስብሰባዎች በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቁ ድጋፉን ይሰጣል።

በዚሁ አጋጣሚም የመድረክ አመራር አባላት በዲያስፓራ በሰሜን አሜሪካ ያቀዱትን ስብሰባዎች የተሳካ እንዲሆን፣ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ የጀመሩትን ውስብሰብ የፓለቲካ ትግል እንዲጠነክር፣ የድርጅታቸውን የመንቀሳቀስ ዓቅም እንዲጎለብትና የእንቅስቃሴያቸውን አድማስ እንዲሰፋ፣ እንዲሁም ሀገርንና ህዝብን ማእከል ባደረጉ ጉዳዮች ዙሪያ ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል። ሌሎቻችን በዲያስፓራ የምንገኝ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንም ጥቃቅን ልዩነቶችንን ወደ ጎን ትተን በዋናው ሀገራዊና ህዝባዊ ጉዳይ በማትኮር የህዝባችን ትግል ፈር እንዲይዝና ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የምንፈልግ ሁሉ በተጠሩት ስብሰባዎች በመገኘት ከኛ የሚፈለገውን ተሳትፎ እንድናደርግላቸው ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በመጨረሻም በሀገር ውስጥ ሰላማዊና ሕጋዊ የትግል መንገድ በመከተል በስልጣን ላይ ካለው አምባ ገነናዊ ስርዓት የምትጋፈጡ መላ የመድረክና ሌሎች ዲሞክራሲያን ሀይሎች አባላት፣ በእስር በጨለማ ቤት ታጉራችሁ የምትሰቃዩ ወገኖቻችን፣ በንሮ ውድነትና በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ የሚገኘው መላ ህዝባችን የሚደርስባችሁ አፈና የዲሞክራሲ፣ የነፃነትና የፍትሕ ዋጋ ነውና ፅናታችሁን እናደንቃለን። የምታደርጉት ሀቀኛ ትግልም ምን ያህል እልህ አስጨራሽና መስዋእትነትን የሚጠይቅ መሆኑንም በሚገባ እንረዳለን። በመሆኑም የጋራ ጠላታችን የሆነው ጭቆናና አፈና ከሀገራችን እስከሚወገድ ድረስ ዛሬም እንደ ትናንቱ ማርች ፎር ፍሪደም ከጎናችሁ እንደሚቆም ድጋሚ ያረጋግጣል።

ማርች ፎር ፍሪደም
ስልክ ቁጥር 202-656-8070
ኢሜል: joinUS@march4freedom.org
ዋሽንግተን ዲሲ